
በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



ከኦክቶበር 21-31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና ከኦክቶበር 1-31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም ከኖቬምበር 1-10፣11-20/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ እና ከኖቬምበር 1-30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2026


አዲስ አበባ

1. እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ምስራቅ ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ25 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ ከነበረዉ ከባድ ዝናብ ጋር በተያያዘ በሰሜን ጎንደር ዞን በጃናሞራ ወረዳ በሳቅላ ቀበሌ፤ በደባርቅ ወረዳ አበርጊና እና አርግንጆና ቀበሌዎች፤ በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ጭልጋ ወረዳ በሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች በረዶ ቀላቅሎ የጣለዉ ዝናብ በሰብሎች ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡

በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 39.3-68.8 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች ጉራ በቀርሳ 68.8፣ ዲመካ 67.2፣ ጅማ 57፣ ደብረ ሲና 55.7፣ ዳሊፋጊ 48.2፣ ጅንካ 47.2፣ ዶላ 46.4፣ ጭራ 46፣ ሺንዲ 43.7 ሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች (በሚሊ ሜትር)




ምስል1: ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ ጉጂ፣ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ፣ ነንብ፣ እና ጃረር ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑ ዞኖች ምዕራብ ወለጋ፣ የቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች፤ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የአኝዋክ፣ መኸርንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤ የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች ላይ ከ10-120 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)። በተጨማሪም የሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ ጎጃም፤ የምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ እና ባሌ ዞኖች፤ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የመካከለኛ ትግራይ ዞኖች፤ ቅልበቲ፣ ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሃሪ፣ ጋቢ ዞኖች ከ5-20 ሚ.ሜ የሚደርስ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)።


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ፣ ነንብ፣ እና ጃረር ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑ ዞኖች የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ ዞኖች፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የአኝዋክ፣ መኸርንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)።



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

1.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በቦረና፣ በጉጂ እና በደቡብ ክልል ደቡባዊ ዞኖች የነበረው እርጥበት ለተዘሩ የበጋ ሰብሎች እድገት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ሲሆን፤ በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ለሚገኙ አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማችት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። በአንጻሩም ከክረምት ጀምሮ ዝናብ እያገኙ በነበሩት በደቡብ ምዕራብ አጋማሽ የመኸር ሰብል አብቃይ አከባቢዎች የተገኘው እርጥበት ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በማፍራትና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለነበሩ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እና ለፍራፍሬዎች የተሟላ እድገት እንዲኖራቸዉ ከማድረግ አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ እንዲሁም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልባቸዉ የሰሜን፣ ሰሜን ምስራቅ፣ መካከለኛዉ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች አልፎ አልፎ የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ እና ስንዴ በመሳሰሉ ሰብሎች ላይ መጠነኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ የነበረው ሲሆን ዘግይተዉ ለተዘሩ ሰብሎች ግን ፍሪ ለማፍራት አዎንታዊ ሚና ነበረዉ (ካርታ 4)።

1.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፈናቸው ቀናቶች በአብዛኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ኡጋዴን ገናሌ ዳዋ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በመካከለኛ ተከዜ፣ እንዲሁም መካከለኛና ላይኛው አባይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ደግሞ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውኃ ነበረው፡፡ በመሆኑም ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት ገብዓት ጥሩ አስተዋፅየ እንደነበረው የተተነተኑ የሀይድሮ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ይህ ሁኔታ በተለይም ዋንኛ ወቅታችው ለሆኑት ለአብዛኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኡጋዴን ለመካከለኛና ታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ ጠቀሜታው እጅግ የጎላ ነው (ካርታ 5)።



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


1.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ

ባለፈዉ ወር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታችዉ በሆኑት በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ምስራቅና ሰሜን ምስራቅ ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ሰሜን ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ ወር በ57 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30

ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)። ከነበረዉ ከባድ ዝናብ ጋር በተያያዘ በሰሜን ጎንደር ዞን በጃናሞራ ወረደ በሳቅባ ቀበሌ፤ በደባርቅ ወረዳ አበርጊና እና አርግንጆና ቀበሌዎች፤ በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ጭልጋ ወረዳ በሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች በረዶ ቀላቅሎ የጣለዉ ዝናብ በሰብሎች ላይ ጉዳት አድርሷል። እንዲሁም በመልካ ዲዳ፣ በቀላፎ፣ በጎዴ እና በፋፈን አካባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ተከስቷል።

በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብና ደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ40-119 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መንደር11 119.0፣ ድሬ ሸኸና ሁሴን 85.5፣ አርባ ምንጭ 73.2፣ ጉራ በቀርሳ 68.8፣ ጎዴ 68፣ ዲመካ 67.2፣ አዴት 60፣ መርሳ 57.4፣ ጅማ 57፣ ደብርሲና 55.7፣ ጊኒር 54 ሚ.ሜ ይገኙበታል።


ከአክቶበር 1 እስከ 31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች (በሚሊ ሜትር)




ምስል2: ከአክቶበር 1 እስከ 31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ባለፈዉ የኦክቶበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ ጉጂ፣ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ፣ ነጎብ፣ እና ጃረር ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑ ዞኖች ምዕራብ ወለጋ፣ የቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች፤ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የአኝዋክ፣ መኾንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች ላይ ከ30-300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ6-22 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7)። በተጨማሪም የሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ ጎጃም፤ የምዕራብ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ እና ባሌ ዞኖች ፤የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የመካከለኛ ትግራይ ዞኖች፤ ቅልበቲ፣ ፋንቲ፣ ማሂ፣ ሃሪ፣ ጋቢ ዞኖች ከ15-50 ሚ.ሜ የሚደርስ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ዝናብ ከ4-12 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 6 እና 7)።


ባለፈዉ የኦክቶበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ፣ ነጎብ፣ እና ጃረር ዞኖች፤ የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ እንዲሁም የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑ ዞኖች የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ዞኖች፤ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፤ የአኝዋክ፣ መኾንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች፤ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፤የወላይታ፣ ጎፋ እና ጌድዮ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 8)።



ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026
የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

1.3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ በኦክቶበር ወር የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አካባቢዎች በተለይም በቦረና፣ ጉጂ እና የደቡብ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ለሚካሄደው የሰብል ልማት የማሳ ዝግጅት ለማድርግ፣ ዘር ለመዝራትና ለተዘሩ ሰብሎች እድገት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል። በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብና ምዕራብ አጋማሽ በሚገኙ የሀገራችን አካባቢዎች ተጨማሪ እርጥበት ለሚያስፈልጋቸው እና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። በመሆኑም በዚህ ወቅት የተገኘው እርጥበት በተለይም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። በሌላ በኩል በሰሜን፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው እርጥበት ዘግይተው ተዘርተው ዕድገታቸውን ላልጨረሱና ከመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ በአፈር ውስጥ በሚገኝ እርጥበት ለተዘሩ እንደ ሽንብራና ጓያ ላሉ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለፍራፍሬዎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር አዎንታዊ ጎን ነበረው። በአንጻሩ ግን በተለይም በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ እንዲሁም በአንዳንድ የመካከለኛው የሀገራችን አካባቢዎች በወሩ መጨረሻ ላይ የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በመኸር ሰብል ስብሰባ ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ተጽዕኖ ነበረው(ካርታ 9)።


1.4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፈው የኦክቶበር ወር በአብዛኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ እንዲሁም በመካከለኛና በመካከለኛ ተከዜ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት የነበራቸው።በተጨማሪም በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆና ላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ደግሞ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውኃ ነበረው። ይህ ሁኔታ በተለይም ዋነኛ ወቅታቸው ለሆኑት ለአብዛኛው የዋቤ ሸበሌ፣ የገናሌ ዳዋ፣ የኦጋዴን፣ ለመካከለኛና ታችኛው ኦሞ ጊቤ እንዲሁም ለስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የሚኖረው ጠቀሜታ እጅግ የጎላ ነው። በተለይም እንደ ዋቤ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ መካከለኛና ታችኛው ኦሞ ጊቤ እና ስምጥ ሸለቆ ላሉ ዋና ዋና ወቅታዊ የውሃ ተፋሰሶችና አካባቢዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለነዚህ ክፍሎች ያለው ፋይዳ እጅግ የላቀ ነው (ካርታ 10)።



ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 31/2026

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


2. መግቢያ

በኖቬምበር ወር የበጋው ዝናብ በአብዛኛዉ በደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ላይ የሚወሰን በመሆኑ የደቡብ ኦሮሚያ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች ከ5-10 ቀናት ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን በመጠን ከ 50-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል ከ5-10 ቀናት ዝናብ ያገኛሉ። በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በይበልጥ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይስተዋላል፡ ፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ይሄዳሉ፡፡


2.1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 11)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ፣ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 11)፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በሰሜን ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች አነስተኛ መጠን ያለው ወቅቱን

ያልጠበቀ ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 11)። ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል። በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአደሌ፣ አስጎሪ፣ ጫጫ፣ ደብረብርሃን፣ ደሴ፣ ዲክሲስ፣ ዲንሾ፣ ገራዶ፣ ጊምቢ፣ ጊንጩ፣ ጊሸን፣ ጊሸራቤል፣ ጉጉፍቱ፣ ጉንዶ በረት፣ ሆለታ፣ ኪሞዬ እና ቆቱ ላይ በአብዛኛዉ ቀናቶች ለይ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 12)፡



ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-10/2026
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-10/2026
የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን


በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች		
ክልል	ዞን	በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን
አሮሚያ	የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ እና ነጎብ፣ ጃረር፣ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ዞኖች		
አሮሚያ	ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሊአባቦራ፣ ጅማ እና ምዕራብ አርሲ	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ቤንሻንጉል ጉምዝ	የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ቀላል መጠን ያለው ዝናብ (ከ 1-10ሚ.ሜ)
ጋምቤላ	የአኝዋክ፣ መኸንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ)
አማራ	የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ ጎጃም እና የአዊ ዞኖች	ቀላል መጠን ያለው ዝናብ (ከ 1-10ሚ.ሜ)
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ)

ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች		
አማራ	የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ ጎጃም፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)
አሮሚያ	የምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ የሰሜን እና የምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)
ትግራይ	የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች	አነስተኛ መጠን
ሶማሌ	የሲቲ፣ ፋፊን እና ኤረር ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)
ድሬዳዋ እና ሐረሪ		ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)

2.2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዉቹ የኖቬምበር የሁለተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከመጀመሪያው አስር ቀናት የተሻለ መጠንና ስርጭት እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተለይም በደቡባዊው አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት ሰፊ ቦታዎችን የሚያካትትና ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ ይጠበቃል (ካርታ 13)፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና የምስራቅ ቦረና፣ የምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀጣይነት ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ሀይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ፣ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 13)፡፡ በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ

የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆንና፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት እንደሚጠናከር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።




ካርታ 13 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2026, **የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ**


2.3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ከማመዘኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ የሚስተዋልበት ወር ነው፡፡ በሌላ በኩል በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

በሚቀጥለው የኖቬምበር ወር ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከመጀመሪያዉ ሳምንት ጀምሮ በአንፃራዊ ሁኔታ እየተሻሻሉ እንደሚሄድና እስከ ወሩ መጨረሻ ደረስ ቀጣይነት የሚኖራቸዉ ሲሆን፣ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና የምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀጣይነት ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 14 እና 15)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 14 እና1 5)፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ። ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡



ካርታ 14 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር



ካርታ 15 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

2.4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለት የኖቬምበር የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገራችን አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። እንድሁም በ2 ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ባሌ፣ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ያገኛሉ። እንድሁም አልፎ አልፎ በሰሜን ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጥን ያለዉ እርጥበት ይኖራል። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና

አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከታች የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2)።

2.5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው ወር በተለይም የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የመሚኖረው እርጥበት በተለያየ ምክንያት ዘግይተው ለተዘሩና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎችና ፍርፍሬዎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ ፣ምስራቅ ባሌ፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንሰሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ከፍተኛ ጠቀሜታ ከመኖሩም በተጨማሪ የበጋ ሰብል በሚያመርቱ እንደ ቦረናና ጉጂ ለመሳሰሉ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም የሚገኘው እርጥበት በተለይም ውሃ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውሃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የሚፈጥር በመሆኑ ማህበረሰቡ እና የሚመለከታቸው አካላት ይህንን ለማከናወን የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በአንጻሩ ግን የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ በምስራቅ፣ ሰሜን ምስራቅ እና ሰሜን ምዕራብ የሀገራችን አካባቢዎች ሊኖር የሚችለው ቀላል መጠን ያለዉ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለይም በደረሱ እና በመሰብሰብ ላይ በሚገኙ እንደ ሰሊጥ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ አጃ እና ስንዴ እንዲሁም ቀድመው በሚደርሱ እንደ በቆሎ እና ማሽላ የመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ስለሚችል አርሶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት በየጣልቃው የሚኖረውን ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ መሰብሰብ ያስፈልጋል። በተጨማሪም አልፎ አልፎ በመካከለኛዉ፣ ሰሜን ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ክስተት በሚጠበቅባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች በሰብሎችና በመስኖ በሚበቅሉ አዝዕርቶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

2.6 እ.አ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በባሮ አኮቦና በላይኛው ኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ላይ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይጠበቃል። በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በአባይ ተፋሰሶች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ የገጸ ምድር ውሃ ፍሰት የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንፃሩ በተከዜ፣ በመረብ ጋሽ፣ በአዋሽ፣ በአፋር ዳናክልና በላይኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከደረቅ እስከ ቀላል የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል (ሠንጠረዥ 3) ፡፡

2.7 እ.አ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በኖቬምበር ወር በባሮ አኮቦና በላይኛው ኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ላይ ቀደም ብሎ የሚታየው የገጸ መድር የውሃ ፍሰት እንቅስቃሴ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፣ በመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናትም መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይጠበቃል። ከመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት መጨረሻ ጀምሮ የበጋው ሁለተኛ የዝናብ ወቅት በገናሌ ዳዋ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በዋቤ ሸበሌና በኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ እየተጠናከረ የሚሄድ ሲሆን፤ በተለይም በገናሌ ዳዋ፣ በስምጥ ሸለቆና በኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት የመኖር ዕድሉ ከፍተኛ ነው። በአንፃሩ በተከዜ፣ በመረብ ጋሽ፣ በአዋሽ፣ በአፋር ዳናክልና በላይኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፣ በአባይ ተፋሰስ ደግሞ በጥቂት ገባር ወንዞች ላይ ብቻ ቀላል የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይጠበቃል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

የክረምት እርጥበት ተጠቃሚና የመሸር አምራች ዞኖች			
ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሊአባቦራ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አኝዋክ፣ መዠንግ፣ ኑዌር ፣ የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ ፣ምዕራብ ኦሞ ፣ ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ ሰሜንና ምዕራብ ጎጃም እና አዊ ዞኖች	➢ የአፈር ውስጥ እርጥበት መኖር እንደ ሽንብራና ጓያ የመሳሰሉ በክረምቱ መጨረሻ ላይ ለተዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች እድገት ➢ ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች ፍሪ ለማፍራት ➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት ➢ ለቋሚ ተክሎች እና ለግጦሽ ሳር ዕድገት ➢ ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ	➢ የደረሱ ሰብሎች ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መኖር ➢ ከእርጥበትና ሙቀት የተነሳ የዋግ በሽታ መከሰት	➢ የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች መሰብሰብ ➢ የሰብል በሽታን አስቀድሞ መከላከል ➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም ➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ ➢ የጥራጥሬ ሰብሎች (ሽንብራ እና ጓያ) እድገትን መከታተል

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች			
ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ ፣ምስራቅ ባሌ፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ዶሎ ፣ ነንብ፣ ጃረር፣ ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ ፣ ደቡብ ኦሞ ፣ የሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች	➢ በጋ ተጠቃሚ በሆኑ ደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገት ➢ ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል ➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም	➢ የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት ፤ ➢ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና ➢ የእርጥበት ትነት መኖር	➢ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም ➢ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ለተዘሩ ሰብሎች የአረም ማስወገድ ስራዎችን መስራት ➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል ➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤
ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚ ጠበቅባቸው ዞኖች			
ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ

የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምስራቅ ጎጃም፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ፣ አርሲ ፣ምዕራብ አርሲ፣ ሰሜን እና ምዕራብ የሸዋ፣ ባሌ ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ፣ ሲቲ፣ ፋፈን ፣ ኤረር፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ	➢ ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት ➢ ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት ➢ በበጋ መስኖ ለሚከናውን የግብርና እንቅስቃሴ	በደረሱ የመኸር ሰብል ስብሰባ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መኖር	የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ማከናወን

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
• ባሮ አኮቦ • ላይኛው ኦሞ ጊቤ	• የወንዞችና የግድቦች የውሃ መጠን መጨመር • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ የውሃ ክምችት መሻሻል • የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት መጨመር	• የአፈር መሸርሸርና የደለል ስጋት	የዝናብ ውሃ ማሰባሰብና የግድቦችን የውሃ መጠን መከታተል
ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ**
• ታችኛው ኦሞ ጊቤ • ስምጥ ሸለቆ • ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌና አጋይን • በጥቂት የአባይ ተፋሰሶች ላይ	• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል • የወንዞችና የትናንሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎች መጠነኛ መሙላት	• ከፍተኛ ትነት መኖር	• የዝናብ ውሃ ከጣራና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ • የውሃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም • የፍሳሽ መውረጃዎችን ማፅዳት
ደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት	**አዎንታዊ ተጽዕኖ**	**አሉታዊ ተጽዕኖ**	**የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ**
• ተከዜና መረብ ጋሽ • አዋሽ • አፋር ዳናክል • ላይኛው ዋቤ ሸበሌ	• የጎርፍና የደለል ስጋት አለመኖር	በትነት የውሃ መጠን መቀነስ	• የሚገኘውን የውሃ ሀብት በአግባቡ መጠቀም • መጠነኛ የዝናብ ውሃ ማሰባሰብና ከብክነትና ከብክለት መከላከል • ለደረቅ ወቅት የውሃ አቅርቦት መዘጋጀት